

# አሁን ዳግመኛ ተወልደሀል

*ክሪስ ኦያክሒሎም*

Now That You Are Born Again

# አሁን ዳግመኛ ተወልደሀል


መጋቢ ክሪስ ኦያክሒሎም
Pastor Chris Oyakhilome


ተርጓሚ መስፍን ሓጎስ ተወልደ

ካልተገለጸ በስተቀር በዚህ እትም ዉስጥ፡የተጠቀሱት ጥቅሶች በሙሉ ከኪንግ ጀምስ
መጽሓፍ  ቅዱስ እትም የተወሰዱ ናቸው።

ሁለተኛው እትም 2003

ISBN 978 - 34658-7-2

Published by:

LoveWorld Publications BLW Inc.

**UNITED KINGDOM**:
Christ Embassy Int'l Office
Suite 209/210 Estuary House
Ballards Road
Dagenham RM10 9 AB
P.O. Box 21520
London, E10 5FG
Tel: 44-208-517 2367

**NIGERIA**:
P.O. Box 13563
Ikeja, Lagos
Tel: 234-1-774 0109 / 774 0243
234-802 3324 187-9

**USA:**
Executive Building
7100 Baltimore Avenue
Suite 211, College Park,
Maryland 20740
Tel: 1-301-985 9200

ኢ-ሜይል :cec@christembassy.org
ድህረ ገጽ :www.christembassy.org

© Copyright 1999
LoveWorld Publications

የደራሲዉ  መብት የተጠበቀ ነው። ከአሳታሚው ድርጅት  ፈቃድ በጽሁፍ ካልተሰጠ በስተቀር፣  በተናጠል  ወይም
በሙሉ ማባዛት የተከለከለ ነው።

Translated

By Mesfin Hagos Tewolde

(*Fribourg, Switzerland*)

2012

ተርጓሚ፣

መስፍን ሓጎስ ተወልደ
(*ፍሪቦርግ፣ ስዊዘርላንድ*)
2012

civileng.ch

## ማዉጫ

1 እዉነተኛው አንተ ........................................ 3

2 አንተ አዲስ ፍጡር ነህ ........................................ 5

3 የእግዚአብሔር ባሕርይና ሕይወት በዉስጥህ አለ ........................................ 6

4 የእግዚአብሔር ጽድቅ ነህ ........................................ 8

5 በደልህ ተሠርዟል ........................................ 9

6 ተቀድሰኃል ........................................ 10

7 አርነት ወጥተኃል ........................................ 11

8 የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥህ ይኖራል ........................................ 12

9 የተሳሣተ ሓሳብ በአእምሮህ ሲመላለስ ምን ታደርጋለህ ....? ........................................ 13

10 የቀድሞ ጓደኞችህ ተስፋ ለማስቆረጥ በሚጥሩ ግዜ ምን ታደርጋለህ? ........................................ 17

11 መከራና ሓዘን በሆነ ግዜ ምን ታደርጋለህ? ........................................ 19

12 መንፈስ ቅዱስና አንተ ........................................ 22

13 ወደ ቤተ ክርስቲያን ልትሄድ ይገባል ........................................ 26



## *ዉድ የምወድህ፣*

እየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታህ እና አዳኝህ አድርገህ በመቀበልህ በነጻ ስለ አገኘኸው ዘላለማዊ መዳን እንኳን ደስ አለህ።

ለክርስቲያን ሕይወት መሰረት የሆነውን እዉነት ላንተ ማካፈልን እወዳለሁ ፡፡ በዚህም ጠንካራና ትርጉም ያለው ሕይወት ልትመሰርት ትችላለህ። ይህንን ጽሁፍ በትጋት አጥና እናም ፣ ዘላለማዊ ምርት ያፈራልኃል።

ስለእርሱ ታዉቅ ዘንድ፣ የጥበብ መንፈስና መገለጥን እንዲሰጥህ እጸልያለሁ። የመረዳት አይኖችህ እንዲገለጡና ለትልቅ ተስፋ እንደተጠራህና ሁሉም ነገር በክርስቶስ በነጻ እንደተሰጠህ ታዉቃለህ ፣ አሜን።

ይህ ጽሁፍ በክርስቶስ እየሱስ አዲስ ሕይወት እንድትጀምር ያግዝኃል፣ በምታጠናበት ወቅትም መጽሓፍ ቅዱስህን ተመልከት፣ ቃሉንም በራስህ አጥና።

በዉስጡ ያለው መልዕክት ሕይወትህን እንደሚቀይረውና የወደፊት ሕይወትህን በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ቅርጽ ለማስያዝ እንደሚያግዝህ እምነቴ ነው።

እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክህ፣ በእየሱስ ስም፣
አሜን ፡፡

መጋቢ ክሪስ አያክሒሎም
1999

# 1 እዉነተኛው አንተ

አንተ ከምታየው ሰዉነትህ ወይም አካልህ እጅግ ትበልጣለህ። የስሜት ሕዋሳቶችህ መኖሪያ ከሆነው አካልህ በላይ ነህ (የማየት፣ የመስማት፣ የመዳሰስ፣ የመቅመስና የማሽተት ስሜት ሕዋሳቶችህን ከሚያኖረው አካልህ በላይ)። በውስጥህ፣ ከአካልህ የሚበልጥ ነገር አለ:: ይህም መንፈስ ነው፣ እናም ይህ እውነተኛው ሰው ነው። ይህ የውስጠኛውን ሰው ነው መጽሓፍ ቅዱስ 1 ኛ ጴጥሮስ 3:4 “***ነገር ግን በልብ ዉስጥ ተሸፍኖ እንደሚኖር ሰው፣ በዛም የማይለወጥ፣ እጅግ በጣም ታጋሽና ዝግተኛ መንፈስ***” ሲል የሚጠቅሰው።

የሰዉ አካል በሞተበት ጊዜ፣ መንፈሱ ይኖራል። እሱም ከመሞቱ በፊት የነበረውን ሰው ይመስላል። በምድር ላይ በአካል የመንቀሳቀስ ችሎታዉን ከማጣቱ በስተቀረ ፣ ምንም የሚያጣዉ ነገር አይኖርም። ሰዉነቱ (ስጋው) ሞቶ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን እዉነተኛው ሰው ወይም መንፈሱ ከመሞቱ በፊት የነበረው ዕዉቀት አሁንም ይኖረዋል።

እየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል በሉቃስ 16 ስለ ሁለት የሞቱ ሰዎች ይናገራል። አንደኛው አልዓዛር የሚባል ተመፅዋች ነበር። ቁም ነገሩ ተመፅዋች ስለ ነበር አይደለም፣ ነገር ግን ደሃ ሰው ቢሆንም በጻድቃን መሰማቱ ነው። በሞተም ጊዜ፣ ወደ አብርሃም እቅፍ ተወሰደ። ሁለተኛዉም ሰው ሞተ። ይህኛው ሰው በምድር ሳለ ባለ ጸጋ ነበረ፣ ነገር ግን በምድር ሳለ ሁሉም ነገር ቢኖረዉም የጻድቅ ሕይወት እይኖርም ነበር።

በሞተም ጊዜ ስጋው ወይም ሰዉነቱ ምድር ላይ እንደተቀበረ ብንገነዘብም፣ እየሱስ እንዳለው፣ ባለ ጸጋ የነበረዉ ሰው፣ በገኃነብ እሳት ዉስጥ ሆኖ ወደላይ አሻቅቦ አልዓዛርን በአብርሃም እቅፍ ሆኖ አየዉ፣ አልዓዛርንም አወቀው። ይህም ማለት ይህ ሰው እስካሁን ማየት ይችላል። ከዚያም አብርሃምን እባክህን እርዳኝ ሲል ጮሆ ተጣራ (ተመልከት፣ ይህ ሰው እስካሁን መናገር ይችላል)። አብርሃምም መለሰለትና ድምፁን ሰማ፣ ይህም ማለት ይህ ሰው እስካሁን ማዳመጥ ይችላል። ሰውዬዉም እንደጠማው ተናገረ፣ መጠማቱ ብቻ ሳይሆን የነበረበት ቦታም ደረቅ ነበረ። ሰዉዬዉም እንዲህ ሲል ለመነ ‘’***አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ሲደድልኝ አለ***”። አሁንም ሌላ ነጥብ ብንመለከት፣ ሰዉዬው እስካሁን ስሜት አለው።



ሁሉም ሕዋሳቶቹ እንዳሉ አሉ። በርግጥም፣ ማስታወስ ይችል ነበር ምክንያቱም እባክህን፣ ከሞቱት መካከል አንድ ሰው ፥ ወደ ወንድሞቼ ላክና ይመስክርላቸው ብሎ ነበር ። እንዲህ ነበር ያለው ‘’***ምናልባት ከሞቱት መካከል ወደ እነርሱ ቢሄድ ያምናሉ አለ***” ። እርሱም አስታወሰ !

ይህ፣ ሰው ከሞተ በኋላ መንፈሱ እንደሚኖር ያስረዳናል። እናም ሰው በክርስቶስ ዳግመኛ ሲወለድ ፣ መንፈሱ ነው እንደገና የሚወለደው። 2 ኛ ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች 5: 17-18 (KJV) እንዲህ ይላል ‘’***ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው***”።

# 2 አንተ አዲስ ፍጡር ነህ

አሁን ሕይወትህን ለእየሱስ ክርስቶስ ሰጥተሃል፣ የሕይወትህ ጌታ አድርገኸዋል። በፊት እንደነበርከው አይደለህም። በዉጪ ስትታይ እንደቀድሞው ትመስል ይሆናል፣ ነገር ግን በውስጥህ ሙሉ በሙሉ አዲስ ፍጡር ነህ። መጽሓፍ ቅዱስ እንዲሁ ነው የሚለው። እዲስ ፍጡር የምትመስል አይደለህም፣ ነገር ግን አዲስ ፍጡር ነህ፤ አዲስ ዘር፣ ከዚህ በፊት በጭራሽ ያልነበረ (2ኛ ቆሮንጦስ 5,17 kjv).

እንደገና የተጠገንክ፣ የተጌጥክ ወይም የታደስክ አይደለህም። አዲስ ፍጡር ነህ። ሙሉ በሙሉ አዲስ ፍጡር። ይህም ማለት፣ በርግጥ በዉስጥህ አዲስ ፍጡር ብትሆንም፣ በዉጪ ትቀየራለህ ማለት አይደለም። ዳግመኛ በክርስቶስ ከመወለድህ በፊት፣ ጸጉርህን በአጭሩ ተቆርጠኸው ከነበረ፣ አሁንም አጭር ጸጉርህ እንደነበረ ይሆናል፣ አይቀየርም። ስራህም፣ ቤተሰቦችህና ጎረቤቶችህም አይቀየሩም። ዋናው ነጥብ፡ አሁን ግንዛቤዎችህ ተቀይረዋል። አዲስ መለኪያዎች (ግንዛቤዎች) ይኖሩኃል፣ ምክንያቱም በዉስጥህ ያለዉ አዲስ ፍጡር ስለሆነ።



# 3 የእግዚአብሔር ባሕርይና ሕይወት በዉስጥህ አለ

በክርስቶስ እንደገና በመወለድህ፣ እግዚአብሔር ልጁ እንድትሆን ሥልጣን ሰጥቶኃል (ዮሓንስ 1:12)። የእግዚአብሔር ባሕርይ በዉስጥህ ሰርጾዋል። አሁን ያለህ ሕይወት አዲስ ሕይወት ነው፣ ይህም እየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ እንዲያገኙ ያደረገው የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። እጅግ ታላቅ እድል! ፣ ስለዚህ እናንተ የእግዚአብሔር ባሕርያት ተካፋዮች ናችሁ (2ኛ ጴጥሮስ 1:3–4)።

አሁን እግዚአብሔር አባትህ ነው! እንዴት ብንል? ተፈጥሮ እራሱን የሚተካው(የሚያራባው) በመዉለድ ስለሆነ፣ ለዛም ነው ዉሻ ሁልጊዜ ዉሻ የሚወልደው። የዮሓንስ ወንጌል 1:12-13 እንዲህ ይላል ***''ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም''***።

እግዚአብሔር ላንተ የአባትነት ተፈጥሮዋዊ ባህርይ አለው። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ትሆናለህ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር በሚኖርበት፣ በመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ትሆናለህ። እሱም ባንተ ላይ ሓላፊነት አለበት። እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል (ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 4:19)። ዳግመኛ በተወለድክ ግዜ የሚጀምር ያማረ ዕቅድ አለዉ ። ፍቅር ለሆነው እግዚአብሔር ዉድ ልጁ ነህ፣ ፍቅር ከሆነ ቤተሰብም ተወልደሀል። ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እርሱም ይህንን አዲስ ሕይወት የሰጠህ የእግዚአብሔር መንግስት አባል መሆን እንድትችል ነው።

መጽሓፍ ቅዱስ ዘላለማዊ ሕይወት እንደተሰጠህ ያዉጃል። ይህ ደሞ በእግዚአብሔር ዉስጥ ያለ ሕይወት ነው፣ ይህም ባሕሪዉ ነው እርሱ የሆነውን እንዲሆን ያደረገው። ይህ የእግዚአብሔር አይነት ሕይወት ነው። ይህ እየሱስ ክርስቶስን ከመቃብሩ ዉስጥ ያስነሣ ባህርይ ነው። ይህ ከሞት የመነሣት ሕይወት ነው! እናም ይህ ሕይወት አሁን ባንተ ዉስጥ አለ።

***''እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ''***(1 ዮሓንስ ምዕራፍ 1:11-13) ።

ልጁ ያለው ብቻ ነው የእግዚአብሔር ሕይወት ያለው፣ ምክንያቱም የእርሱ ሕይወት በልጁ ዉስጥ ስላለ። ልጁን ስትቀበል የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ።

ይህ ሕይወት በምንም ነገር እንዳትሸነፍ ያደርጋል። ሁልግዜም ከፍ አድርጎ ያኖርኃል።እስኪ አስበው! እግዚአብሔር ሊሸነፍ ወይም ብጭራሽ ሊረታ አይቻልም። አሁን አንተም ይህ ሕይወት አለህ። ልትሸነፍ ወይም ልትረታ አትችልም፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ ፣ ባንተ ዉስጥም ስለሚኖር (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:11)።



# 4 የእግዚአብሔር ጽድቅ ነህ

2ኛ ወደቆሮንጦስ ሰዎች 5:21 እንደሚለው ***''እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው''*** ።

አስተዉል፣ እግዚአብሔር ያደረገው እንደ ተፈጥሮዋዊ ዝዉውር (Natural-transplant) ወይም ሽግግር ነው፡፡ እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።

ይህ ነው ኢየሱስን ባንተ ቦታ የኃጢአተኛ ሞት እንዲሞት ያደረገው። ዉጤቱም፣ አንተ አሁን በግዚአብሔር ፊት ያለምንም በደል፣ ፍራቻ ወይም የዝቅተኝነት ስሜት ሳይኖርህ በፊቱ እንድትቀርብ አስችሎኃል (ዕብራዊያን 10:19 ፣ወደ ሮሜ ሰዎች 5:1)።

# 5 በደልህ ተሠርዟል

ምን ማለት ነው በደልህ ተሰርዟል ማለት? ይህ ማለት በደለኛ እንዳልሆንክ ታዉጆዋል ማለት ነው ። በእግዚአብሔር በኩል ከበደልህ ሁሉ ነጻ ነህ። መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው ***‘’እንግዲህ በእምነት ከጻደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ‘’*** (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:1)፤ *በእምነት ጻድቀኃል።*

ኢየሱስ ቅጣቱን ስለናንተ ኃጢአት ሲል በመስቀል ላይ ተቀብሏል ነገር ግን እርሱ ኃጢአት አላደረገም (1ኛ ጴጥሮስ 2:22)። እግዚአብሔር ኃጢኣትህን ይቅር ብሎኋል። መጽሓፍ ቅዱስም ይላል *‘’ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን ኣይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል ኣኖረ‘’*(ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች ሁለተኛ 5: 19)።



# 6 ተቀድሰኃል

ለአፍታ ያህል በጉድጓድ ዉስጥ እንደወደቅክ እናስብ፣ በዛም ሳለህ በጣም በቆሻሻ ተበላሽተኃል፣ አንድ ሰው መጥቶም ከጉድጓድ ዉስጥ ያወጣኃል፡፡ በመቀጠል ማድረግ ያለብህ እራስህን ማጽዳት ነው። በሌላ አባባል ‘’ጉድጓዱን ከላይህ ላይ ማራገፍ ነው’’ ይህ ደግሞ ጊዜና ጥረት ይጠይቃል።

1 ኛ ቆሮንጦስ 6:11 እንዲህ ይላል ***‘’ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል”።***

ቅድስናህ በሁለት እርካብ ነው ያለው፡ መጀመሪያ እግዚአብሔር ከጉድጓድ ዉስጥ አወጣህ፣ ይህ ማለት ዳግመኛ ተወልደሀል ማለት ነው እናም ወዲያዉኑ፣ መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚያዉጀው ተቀድሰኃል ማለት ነው፣ ከዓለም ወደ እግዚአብሔር መጥተኃል። ከዚያም በመቀጠል በእዚአብሔር ቃል በልብህ በመታደስ ልትለወጥና ቆሻሻዉን ከላህይ ላይ ልታራግፍ ይገባሃል (ወደ ሮሜ ሰዎች 12:2)።

በእግዚአብሔር ቃል የመታደሱ ሂደት ቀጣይ ነው። ኣእምሮ በአንድ መንገድ ብቻ እንዲያስብ ሆኖ ነው የተለማመደው። ከማመኑ በፊት ነገሮችን በአካል ማየት ይሻል። አሁን ግን አእምሮን በማደስ ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲመለከት ትፈቅድለታለህ። በእግዚአብሔር አስተያየት መመልከት እንድትችል አእምሮህን እንደገና ታለማምደዋለህ። በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ትናገራለህ፣ በእግዚአብሔር መንገድ ትናገራለህ እናም እርሱ ከቃሉ ዉጤት እንደሚያገኘው አንተም ዉጤት ታገኛለህ።

# 7 አርነት ወጥተኃል

*‘’በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን በማመስገን፥ እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ወደ ሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን”*(ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:12-13)።

ሕይወትህን ለእየሱስ ክርስቶስ ከሰጠህበት ጊዜ ጀምሮ፣ የግእግዚአብሔር መንግስት አባል ሆነሃል። በሌላ አባባል ከገሀነም ደጆች ተፈልፍሎ የወጣ አጋንንት ሊጎዳህ አይችልም። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ቀድሞ ከገባህበት ኪዳን ነጻ ሆነሃል። አስሮ ከያዘህ ካረጀ ልምድ፣ ከኃጢያት፣ ከሕመም ወይም ከደዌ ነጻ ነህ። ለምን? ምክንያቱም ከጨለማው ሥልጣን አርነት ወጥተኃል (ታድገሃል)። መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው እግዚአብሔር ከጨለማ ሥልጣንና ግዛት አውጥቶ ወደ መንግሥቱ አሻግሮናል። ዳግመኛ በጭራሽ ልትፈራ አይገባህም። እግዚአብሔር እረኛህ ነው የመጠበቅ አይኑም ሁል ጊዜ በላይህ ነው (መዝሙረ ዳዊት 23:1)።

መጽሓፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *‘’እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ ‘’* (ዮሓንስ 8:36)*።* እግዚአብሐር ነጻ እንድትሆን ወደ መንግስቱ አምጥቶኃል። እርሱም አሁን ያለህበት ማለት ነው፡ መኖሪያህም በዚሁ ነው። ከጨለማው ሥልጣን ድነሃል (አረፍተ ነገሩን ተመልከት፣ ያለፈን ጊዜ ነው የሚያመለክተው)።



# 8 የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥህ ይኖራል

የአዲሱ ሕይወት ሌላኛው ትልቁ አካል፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥህ ለመኖር ይመጣል። የእግዚአብሔር መንፈስ ባንተ ዉስጥ ስፍራዉን በሚይዝበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በዉስጥህ ያሠርጻል፣ አዲስ መረዳትም ይሰጥሃል።

መጽሓፍ ቅዱስን ስታጠና፣ በመንፈስህ አዲስ መረዳት ይኖረኃል፣ በሕይወትህም ዉስጥ ትጠቀምበታለህ። ሌላው መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ያሳስበሃል (ዮሓንስ 14:26)። በተጨማሪም፣ ኃይልን ትቀበላለህ፥ የእየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ምስክርም ትሆናለህ። *‘’ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ”*(የሓዋርያት ስራ 1:8)።

# 9 የተሳሣተ ሓሳብ በአእምሮህ ሲመላለስ ምን ታደርጋለህ ....?

ዳግመኛ መወለድ ከፈተና አያድንህም፣ ነገር ግን ልትበገር አይገባም፣ መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በፈተና ግዜ፣ እግዚአብሔር መውጫህን ያዘጋጇል (1 ኛ ቆሮንጦስ 10:13)። ስለዚህ የተሳሣተ ሓሳብ በአእምሮህ ሲመላለስ ማድረግ የሚገባህ የሚከተለዉን ነው…

## (1) አዲስ ፍጡር መሆንህን አስታዉስ

እነዚህ አስተሳሰቦች ከዉጪ የመጡ ኃይሎች ናቸው። ከሰይጣን የሆነ ፈተና ነው። ከልብህ ዉስጥ አይመነጩም በተለይ አሁን ዳግመኛ ከተወለድክ በኋላ። መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው (ዳግመኛ የተወለዱ አማኞች) የክርስቶስ ልብ አላቸው ይላል (1 ኛ ቆሮንጦስ 2:16 )። ማን እንደሆንክ ማስታወስ አለብህ፣ አዲስ ፍጡር! እግዚአብሔር ሁልጊዜም አዲስ ፍጡር መሆናችንን እናም እርሱ አዲስ ህይወት እንደሰጠን እንድናስታዉስ ይወዳል። በዚህም አዲስ ህይወት ልታምንበት ይገባል።

## (2) በመታዘዝ ተመላለስ

እግዚአብሔርን ታዘዝ! የመጥፎ ልማድ ሃሳብ በልብህ መጣ እንበል። ይህንን የተሳሣተ ልምድ እንድትፈጽም ሃይለኛ ግፊት ይኖርብህ ይሆናል። ምናልባትም ወደ መጀመሪያው ሁኔታህ ተመልሰህ ይህንን የተሳሣተ ድርጊት ትፈጽም ይሆናል። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ዳግመኛ እንደተወለድክ ካሰብክ፣ አዲስ ሰው መሆንህን ካሰብክ፣ ድንገት ግፊቱን ለማግለል ድፍረቱና ጥንካሬው ይኖርሃል። እግዚአብሔርን ታዘዝ! አየህ፣ ዳግመኛ መወለድ ማለት የተሳሣተ ሃሳብ ወዳንተ አይመጣም ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ባንተ ላይ እንዲጸና ልትፈቅድለት አይገባም። ተቃወመው! አንድ ሰው በትክክል እንደገለጸው፣ *ወፎች በላይህ እንዳይበሩ መከላከል አይቻልም፣ ነገር ግን ጎጆዋቸውን በራስህ ላይ እንዳይሰሩ ግን ማስቆም ትችላለህ።*



እነዚህ የተሳሣቱ ሃሳቦች እንዳይመጡ ማስቆም አትችልም ይሆናል፣ ምክንያቱም የደጅ ኃይል ስለሆኑ፣ ነገር ግን በዉስጥህ እንዳይኖሩ ማድረግ ትችላለህ። የተሳሳተ አስተሳሰብ በልብህ እንዲኖር አትፍቀድለት፣ ዳግም ኃይልና ስልጣን ባንተ ላይ እንዲኖራቸው አትፍቀድ። ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ በማሰብ የተሳሣተውን ሃሳብ ማስወገድ ትችላለህ (ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች 4:8)።

የመድረክ ሥነ ጥበበኛ ነህ እንበል ወይም አቀንቃኝ ። እነደ ሴት ሆነህ ማቀንቀን ትወድ ይሆናል ፣ ነገር ግን በእዉነተኛው ወንድ ነህ። የሴት ልብስ የሆነውን ለብሰሃል፣ ዊግም አድርገኃል። እንደ ሴት ታቀነቅናለህ እንደ ሴትም ትናገራለህ። ነገር ግን ከጨረስክ በኋላ ወንድ መሆንህን አልረሳህም። ከመድረክ ወርደህ ወደ ልብስ መለወጫው ሄድክና ልብስህንም ቀይረህ ወጣህ። ሰኞ ጠዋት ወደ ስራ ልትሄድ ስታስብ፣ በርግጥም ወንድ እንደሆንክ አልረሳህም። እንደወንድም ታወራለህ፣ እንደወንድም ትኖራለህ፣ ስራ ሄደህ ባለፈው ምሽት በመድረክ ላይ ታቀነቅን እንደነበረው፣ እንደሴት ማዉራት፣ እንደ ማላገጥ ይሆንብኃል።

በተመሳሣይ መልኩ። ዳግመኛ ከመወለድህ በፊት በተሳሣተ መንገድ ነበር ታቀነቅን የነበረው ፣ ነገር ግን አሁን አዲስ ሕይወት አለህ፣. አዲሱን ሕይወት ነው መኖር የሚገባህ፡፡ ለረጂም ጊዜ እንደሴት ሆነህ ታቀነቅን ነበር አንዳንዴም መስመርህን ትስታለህ፣ ነገር ግን አንዳንዴ በርግጥም ወንድ መሆንህን ታስታዉሳለህ እናም እራስህን ታስተካክላለህ። ታስተዉልና እንዲህም ትላለህ ‘’ አ ለካስ ሴት አደለሁም በመድረክ ላይ ነው ያለሁት፣ እዉነተኛዉን እኔ መሆን አለብኝ’’ ትላለህ።

መጥፎ ልምድን ማቆሚያ መንድገዱ ይህ ነው። እንዲህም በል *‘’ተመልከት’’ ‘’ዳግመኛ ተወልጃለሁ! ይህ የኔ እዉነተኛው ባህሪዬ ነው ‘’* ምንም አይነት አሮጌ ልምድ ቢኖርህም እንኳን፣ ባስታወስክ ጊዜ (ታስታዉሳለህም). **አቁም**! በል ለራስህ። *ዳግመኛ ተወልጃለሁ! እዛው ላይ አቁም!* ዑደቱ እንዲቀጥል አትፍቀድ እናም ካንተ ጋር በነገሩ ዉስጥ የተሳተፉትን ለመንገር አትፈር *‘’አ በጣም አዝናለሁ ይህንን ላደርግ አልችልም ምክንያቱም ዳግመኛ ተወልጃለሁ በል’’* መጥፎ ልምድን በአዲስ በመተካት አስወግድ። ይህንን ሆነ ብለህ አድርግ ። የእግዚአብሔርን ባሕሪይ ከቃሉ ፈልግ እናም በመደጋገም እራስህን አለማምድ።

## (3) አድራጊ ሁን ፣ እንደ ቃሉ ተግብር

እግዚአብሔር ቃሉን ሰሚ ብቻ እንድንሆን አይወድም ነገር ግን አድራጊዎች እንድንሆን እንጂ ‘’ ***ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ሰሚዎች ብቻ ሆናቹ እራሳችሁን አታታልሉ። ቃሉን የሚሰማ ነገር ግን የማይተገብር ቢኖር ፊቱን በመስተዋት እንደ ሚያይ ሰው ነው፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፥ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸና፥ የሰማዉን የሚያደርግና የማይረሳ ሰው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል”*** (የያዕቆብ መልእክት 1:22̈ -25)።

ቃሉን አስታዉሰህ እንደ ሚለው ከፈጸምክ ቃሉን አድራጊ ትሆናለህ። እናም ሁልጊዜም ቢሆን ታስታዉሳለህ ይህም መንፈስ ቅዱስ በዉስጣችን ሆኖ ከሚያደርገው ከብዙዎቹ አንዱ ነው። እየሱስ እንዳለው *‘’እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል”* (ዮሓንስ 14:26)።
እግዚአብሔር ይመስገን መንፈስ ቅዱስ አሁን ከኛ ጋር አለ፤ ቃሉን እንድናስታዉስ ያግዘናል! ቃሉንም ባስታወስክ ጊዜ፣ ልትፈጽመው ይገባል። ስለማስታወሱ አትጨነቅ ፤መንፈስ ቅዱስ ወደ ማስታወስህ ያመጣኃል፣ ነገር ግን ሁልጊዜ እዉነትን ወደ ልብህ ባመጣበት ጊዜ ልትታዘዘው ዝግጁ ልትሆን ይገባል።

## (4) አስታዉስ ኃጢአት ባንተ ላይ ስልጣን የለዉም

አንድ ነገር ልታስታዉስ ይገባሃል፣ እነዚህ ሃሳቦች ባንተ ላይ እንዲሰለጥኑ ካልፈቀድክላቸው በስተቀረ፣ ምንም ኃይል የላቸውም *‘’ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና’’* (ወደ ሮሜ ሰዎች 6:14)። ኃጢአት ባንተ ላይ ጌትነትን ሊያገኝ አይገባውም፣ የበላይ ስልጣንም አይኖረዉም ምክንያቱም አንተ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለህምና። መጽሓፍ ቅዱስም ይህንን ነው የሚለው ።

እግዚአብሔር ከኃጢአት ስልጣንና ከጨለማው ኃይል አድኖኃል ወደሱም መንግስት አሻግሮኃልና፤ ***‘’በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ወደ ዉድ ልጁ መንግሥትም አሻገረን”*** (ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:12-13) ።



ዳግመኛ ከተወለድክ በኋላ አንተም በዚያ አትኖርም፣ ለዛም ነው የጨለማው ኃይሎች ባንተ ላይ ስልጣን የሌላቸው። ምክንያቱም እነርሱ በኃጢአት ግዛት ዉስጥ ስላሉ፣ አንተ ግን በእግዚአብሔር ግዛት ዉስጥ ስላለህ፣ ይህም ከኃጢአት የበለጠ (የበላይ) ስለሆነ። ስለዚህ አየህ፣ በምንም አይነት ባንተ ላይ ስልጣን አይኖራቸውም ።

ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:14 እንዲህ ይላል፣ ***‘’በእርሱም በደሙ የሆነ መዋጀትን አግኝተናል፣ ይህም የኃጢአት ይቅርታ ነው”*** ። ***‘’በእየሱስ ክርስቶስ ተዋጅተናል ይህም በአሁን ጊዜ ያለን ጸጋ ነው”*** (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:5-6)። ለማግኘት እየጣርን አደለንም፣ አሁን ጸጋው አለን። ይህን የእግዚአብሔርን ቃል ማስታወስ አለብን፣ በዛም ልንጽናና ይገባል።

# 10 የቀድሞ ጓደኞችህ ተስፋ ለማስቆረጥ በሚጥሩ ግዜ ምን ታደርጋለህ?

አሁን ዳግመኛ በመንፈስ ተወልደሀል፣ የአዲስ ቤተሰብ አባል ሆነኃል። ከእንግዲህ ወዲህ የድሮው ቤተሰብ አባል አደለህም። ይህ ማለት ደግሞ የቀድሞ ጉዋደኞችህንና የምታዉቃቸውን ተው ማለት አይደለም፣ ለእነሱ ግን ብርሃን መሆን አለብህ። እነርሱ በጨለማ ዉስጥ ናቸው፣ ምክንያቱም በልባቸው እየሱስ ክርስቶስ የላቸውም። አንተ ለእነርሱ የግዚአብሔር ብርሃን እንደሆንክ ማስታወስ አለብህ"፣ ስለዚህ እነሱም እየሱስን እንዲከተሉ ዕዉቀትህን አካፍላቸው ።

እነዚህ ሰዎች ተስፋ ሊያስቆርጡህ ቢሞክሩ ምን ማደርግ አለብህ? መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው በመጨረሻው ሰዓት የራሳቸውን ክፉ ነገሮች የሚያደርጉ ዘባኞች ይመጣሉ በእዉነትም ላይ ይስቃሉ ( 2 ጴጥሮስ 3:3-4)

ዘባኞች ተስፋ ሊያስቆርጡህ ይሞክራሉ እናም ወደ አሮጌው ሕይወት ይመልሱኃል። ልትቃወማቸው ይገባል፡፡ በዘባኞች ባህርያት ልትሳብ አይገባም፣ ባንተና በእየሱስ ክርስቶስ ዝምድና መካከል እንዳይገቡ ልትቃወማቸውም ይገባል። ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመድ፣ ምክራቸውን አትቀበል። በምትኩ በእግዚአብሔርና በቃሉ ያለህን አቋም አጠናክር።

## የማይመች ጥምድ

እርሻ በማሽን መታረስ ከመጀመሩ በፊት፣ ገበሬ ለማረስ፣ ሁለት እንስሳ ይጠምዳል፣ ለምሳሌ፣ ሁለት አህያ ወይም በሬና ሞፈሩን አገናኝቶ ይጠምዳል፣ እናም ሁለቱ እንሰሳዎች ባንድ ላይ ሲጓዙ መሬቱን ያርሳሉ። ምክንያቱም በአንድ ቀንበር ስር ስለተጠመዱ፡ ሁለቱ እንሰሳዎች በአንድ አቅጣጫ ነው የሚጓዙት፣ አንደኛው ወደ ተጓዘበት ሌላኛውም ይጓዛል። በአንድ ቀንበር ስር እስካሉ ድረስ፣ ገበሬው ወደ መራቸው አቅጣጫ በአንድ ላይ ይጓዛሉ።

ለምሳሌ በቀንበሩ የተጠመዱት ሁለቱም አህያ ከሆኑ የሚመች ጥምድ ይባላል፣ ነገር ግን አንደኛው አህያ ሆኖ ሌላኛው ግን በሬ ከሆነ የማይመች ጥምድ ይባላል፡፡ ከሌላ ሰው ጋር መጠመድ ካለብን የሚመች ጥምድ ሊሆን ይገባል፣ ያም ማለት ክርስቲያንና ክርስቲያን በጓደኛነት ሲጓዙ ማለት



ነው። ነገር ግን ክርስቲያንና የማያምን ሰው ባንድ ላይ ጓደኛ ከሆኑ የማይመች ጥምድ ይሆናል። እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል *''**ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ**''* (2ኛ ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች ሁለተኛ 6: 14-16)።

ስለዚህ አየህ ፣ አንተና የማያምን ሰው ጓደኛ ከሆናቹ ፣ አንድ አይነት ሕይወት የምትኖሩ ከሆነ እንግዲያዉስ በማይመች ቀንበር ስር አላቹህ ማለት ነው፣ እናም ይህ ስህተት ነው። እግዚአብሔር በማይመች ቀንበር ስር እንድትኖር አይወድም፣ ነገር ግን ከሌላ ክርስቲያን ጓደኛህ ጋር በሚመች ቀንበር ዉስጥ አንድ አይነት ነገር እየሰራቹህ እንጂ። የማያምኑ ሰዎች ያንተ ምርጥ ጓደኞች ሊሆኑ አይችሉም። ምንም ግብረገብ ያለው ሰው ቢሆንም እንደገና እስካልተወለደ ግዜ ድረስ ጓደኛህ ሊሆን አይችልም።

በእግዚአብሔር ፊት ይህ የማይቻልና የማይፈቀድ ነው፣ ምክንያቱም የማይመች ቀንበር ስለሆነ። ያንተ ምርጫ ከእግዚአብሔር ምርጫ ጋር አይወዳደርም፡፡ አንድ ግዜ እግዚአብሔር ሳሙኤልን የእስራኤል ንጉስ ይቀባ ዘንድ ወደ እሴይ ቤት ላከው (ሳሙኤል 16:1-13)። ሳሙኤልም የእሴይን የመጀመሪያ ልጅ ፣ኤልያብን፣ ባየ ግዜ እንዲህ አለ *''በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው አለ። ምክንያቱም እሱ በጣም ግዙፍ፣ ረጅምና ቆንጆ ነበረ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለሳሙኤል እንዲህ ሲል ተናገረው ''እርሱን አትቀባ፣ ምክንያቱም አልመረጥኩትም አለ"* ። እንዲህም አለ *''ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው"።* **የዉስጠኛዉን ሰው።** ስለዚህ ያንተ ምርጫ ቢበዛ በ ዉጪኛው ገጽታ የተመረኮዘ ነው የሚሆነው። ምን እንደተናገረ፣ ምን እንደሚመስል ፣ ሌሎችም የመሳሰሉ ግምገማዎችህ ፣ ነገር ግን አየህ እግዚአብሔር የዉስጠኛዉን ገጽታ ነው የሚመለከተው።

ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው መንፈስ ከግዚአብሔር መንፈስ ጋር አብሮ አይሄድም። ብቸኛው መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ መሆን የሚቻለው ዳግመኛ ሲወለድ ነው። በዚህን ጊዜ ብቻ ነው ግለሰቡ ምርጥ ጓደኛህ ሊሆን የሚችለው። ዳግመኛ እስካልተወለደ ድረስ ግን ያንተ ምርጥ ጓደኛ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን መለኪያ ስለማያሟላ ነው። አሁን ዳግመኛ ተወልደሀል ፣ ያንተም ፍላጎት መሆን ያለበት እግዚአብሔርን ማስደሰት ነው፣ ስለዚህ የራስህን መመዘኛ (መገምገሚያ) አትጠቀምም። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ።

ልብህን በቃሉ ላይ አድርግ፣ እርሱ ደግሞ መውጫውን ያደርግልኃል (ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች አንደኛ 10:13)።

# 11 መከራና ሓዘን በሆነ ግዜ ምን ታደርጋለህ?

በማርቆስ ወንጌል 4: 1-9፣ እየሱስ ዘር ስለሚዘራ ሰው በምሳሌ ያስረዳል። ሰዉዬው ዘሩን ዘራ አንዳንዱ በጭንጫ መሬት ወደቀ፣ አንዳንዱ ደግሞ በደረቅ (በመንገድ ዳር) መሬት ወደቀ ፣ አንዳንዱ በቀጋ (በእሾህ) መካከል ወደቀ፣ አንዳንዱ ደሞ በመልካም መሬት ወደቀ። በምዕራፍ 16 ና 17 ፣ መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው ‘’ ***እንዲሁም በጭንጫ ላይ የተዘሩት እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፥ ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ”*** (ማርቆስ ወንጌል 4:16-17)።

እርሱም ስለ ሥር የሌላቸው ሰዎች ነው የሚናገረው፣ መከራ ወይም ስደት በሆነ ግዜ ለተወሰነ ግዜ ብቻ መቋቋም የሚችሉ። እርሱም እንዲህ ይላል ነገር ግን ቃሉን በደስታ ቢቀበሉም በቃሉ ምክንያት መከራና ስደት በሆነ ግዜ ይሰናከላሉ፣ ይህ በብዙ ሰዎች ዘንድ የሆነ ነገር ነው። እየሱስ ክርስቶስ የሚናገረው ብዙ ሰዎች በእርሱ ጥልቅ ፍቅር እንደሌላቸው ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል በጣም ይፈነጥዛሉ፣ ምክንያቱም የዘላለማዊ ሕይወት ቃልኪዳን፣ ፍሥሓና ሌሎችም እንዳሉ ስለተረዱ ነው። ነገር ግን ጥልቅ ፍቅር ለእግዚአብሔር የላቸውም። መከራ ሲመጣ እግዚአብሔርን ይተዋሉ። እንደተባለው! መከራና ስደት ሲመጣ ዓለምን ይከተላሉ።

## (1) ጥልቅ ፍቅር ለእግዚአብሔር ሊኖርህ ይገባል

እግዚአብሔር ለእርሱ ጥልቅና የጠበቀ ፍቅር እንዲኖርህ ይወዳል። ፍቅር ሊጨምር ይችላል ወይም ደግሞ ሊቀንስም ይችላል። ስለእርሱ ብዙ ባሰብክ ግዜ ፣ ቃሉን በሰማህ ግዜ ከሱ ጋራ በጸሎት በተጎዳኘህ ግዜ፣ ለእርሱ የበለጠ ፍቅር ይኖርሃል፣ ምክንያቱም ፍቅር በመቀራረብ ይጨምራልና። ከእርሱ ጋር ብዙ በቀረብክ ግዜ፣ ቃሉን በብዛት በሰማህ ግዜ፣ ብዙ ትወደዋለህ እናም ታዉቀዋለህ፣ ከዛም እርሱን በብዛት ታገኘዋለህ። ጥብቅ ፍቅር ባለህ ግዜ ቃሉ በልብህ ዉስጥ ስሩን ይሰዳል፡ ስለዚህ ምንም አይነት ችግር ቢገጥምህ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የግዚአብሔርን አቋም ታዉቀዋለህ። ወዲያዉኑ፣ የእግዚአብሔርን አቋም በነገሩ ላይ ታዉጃለህ ።



መጽሓፍ ቅዱስ እንደሚለው ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው (መጽሐፈ ምሳሌ 18:20-21)። ደግሞም በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና (የማቴዎስ ወንጌል 12:34-35፣37) ልብህን በእግዚአብሔር ቃል በሞላህ ግዜ፣ ምንም አይነት ችግር ቢገጥምህም እንኳ፣ ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ ትመለከታቸዋለህ እናም እንደ እግዚአብሔር ቃል ትናገራለህ። ችግሩም ያልፋል !

## (2) ተስፋ አትቁረጥ!

ችግር ሲመጣ ተስፋ ልትቆርጥ አይገባም። ዳግመኛ መወለድ ማለት ችግር አይመጣም ማለት አይደለም፣ መከራም የለም ማለት አይደለም። ዳግመኛ መወለድ ማለት ችግር በመጣ ግዜ፣ ሁሉም ችግር እያለ እግዚአብሔር ያስችለኃል ማለት ነው። በመዝሙረ ዳዊት 23:5 እንደተጻፈው ‘’ ***በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው”***። በጠላቶችህ መካከል ብትሆንም እንኳን ሊያሸንፉህ አይችሉም፥ መከራው ሕይወትህን ሊያፈራርስ አይችልም።

እግዚአብሔር ተስፋ እንድትቆርጥ አይወድም። ልትጠነክር ይገባል! አስቸጋሪ ቢመስልም ፣ ተስፋ አትቁረጥ፣ እግዚአብሔር ያሳልፍልሃል። በሆነ ነገር ሁሉ ተስፋ አትቁረጥ፣ በእምነትህ ጽና። እግዚአብሔር በጭራሽ አያሳፍርህም ወይም አይተዉህም፡፡ በሁሉም የሕይወት ሁኔታዎች አሸናፊ ትሆናለህ። ምክንያቱም ሁኔታዎች ላንተ ተገዢ ስለሚሆኑ። ትንቢተ ኢሳይያስ 43:2 እንዲህ ይላል በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድክ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም። እየሱስ ክርስቶስን ተከታይ ሆነህ፣ ዉጊያው ቢበዛም እንኳን በሙሉ ልብህ ልታገለግለው ይገባል።

***‘’ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ ለጌታም ሥራ ሁልጊዜ የምትተጉ ሁኑ”*** (1 ኛ ቆሮንጦስ 15:57-58)።

***‘’ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው”*** (1 ዮሐንስ 5:4) ።

አየህ፣ እግዚአብሔር ድልን በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ ሰጥቶናል። 1 ዮሐንስ 5:4 በጥንቃቄ ተመልከት፣ የሚናገረው ዓለምን ስላሸነፈው ነው፤ ይህም የኛ እምነት ነው። በእምነት ኑር፣ አሸናፊ ነህ፣ ተሸናፊ አደለህም። አሸናፊ ሆነህ ነው የተወለድከው፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ስለተወለድክ፣ የእግዚአብሔር የዘር ሓረግ ስላለህ፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ ስለተወለድክ።



# 12 መንፈስ ቅዱስና አንተ

*''ዳግመኛ መወለድ ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ መወለድ ነው''* (1 ኛ ቆሮንጦስ 12:13፣ ዮሐንስ 3: 5-8) ። *መንፈስ ቅዱስ የሕይወትህ ክፋል ይሆናል፣ ስለዚህ ማን መሆኑን ልታዉቅና ባንተ ሕይወት ዉስጥም ስራዉ ምን እንደሆነ ልታውቅ ይገባል። ምን ሊሰጥህ እንደሚችል ማወቅ አለብህ ። ስለዚህ* በክርስቶስ የሚገኝ የተትረፈረፈና የበዛ ሕይወት እናም ላንተ የሚሆነውን ስጦታም መቀበል ትችላለህ (1 ኛ ቆሮንጦስ 12:8.10) ደግሞም ኃይልን በእርሱ ልትቀበል ትችላለህ (ሉቃስ 24:49 ፣የሓዋርያት ስራ 1:4-8)።

## መንፈስ ቅዱስ ማነው?

በመጽሓፍ ቅዱስ ዉስጥ፡በተለያየ ስፍራ መንፈስ ቅዱስ ተጠቅሶ እናገኛለን :-

- በብሉይ ኪዳን ፣ በኃይል ሲወርድና፤ አስደናቂ ነገሮችን ሲሰራ እናያለን (መጽሐፈ መሣፍንት 14:6 , 19)፣
- በአዲስ ኪዳን ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ በአገልግሎቱና ሕይወቱ ዉስጥ በጣም ጎልቶ እናያለን (ሉቃስ 4:18)፣
- በሓዋርያት ስራ 2:1-4 መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርቱ ሕይወት ስራዉን ሲሰራ እናያለን። እርሱም እግዚአብሔር ነው፣. እርሱም መለኮታዊና የሥላሴ ሶስተኛው አካል ነው (ዮሐንስ 14: 16_17 ፣ ዮሐንስ 15: 26)፣
- ከጊዜ በፊት ቀድሞ ነበር (ኦሪት ዘፍጥረት 1:2)፣
- የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫው ነው። በሌላ አነጋገር፣ እርሱ የእግዚአብሔር አካል ሆኖ፣ እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ የሚፈጽም ነው (ኦሪት ዘፍጥረት 1)፣
- የፍቅር፣ የኃይልና የጥሩ የአእምሮ መንፈስ ነው (2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 1:7)፣እና – እርሱ የአርነት መንፈስ ነው (2 ኛ ቆሮንጦስ 3:17)።

## መንፈስ ቅዱስ ያልሆነው ምንድነው?

በመጽሓፍ እንደተገለጸው መንፈስ ቅዱስ በኃይል፣ በነፋስ፣ በዘይትና በርግብ ተመስሎ ብናይም እርሱ ኃይል፣ ነፋስ፣ ዘይትና ርግብ እንዳልሆነ ማስታወሱ ጥቅም አለው። የመናገር ችሎታ ቢሰጥም፣ እርሱ ምላስ አይደለም። እርሱ ኃይል አደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል ወደኛ ያመጣል። የባርነት መንፈስ አይደለም (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:15)፣ ነገር ግን የአርነት እንጂ (2 ኛ ቆሮንጦስ 3:17)።

## መንፈስ ቅዱስ ለምን ያስፈልገናል?

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ኃይል ይሰጠናል (የሓዋርያት ስራ 1:8)፡ ይህ ቃል ''ኃይል'' ከግሪክ ቃል ''ዱናሚስ'' (Dunamis), የተተረጎመ ነው ፣ ትርጉሙም ለዉጥ:ሊያስገኝ:የሚችል እንቅስቃሴ (ግፊት) ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደኛ ዉስጥ ሊኖር በመጣ ግዜ ። እርሱ በህይወታችን ዉስጥና በሌላ ሰዎች ሕይወት ዉስጥ ነገሮችን የመለወጥ ችሎታን ይሰጠናል ።

- ወንጌልን መስበክ እንድንችል ድፍረቱን ይሰጠናል (የማቴዎስ ወንጌል 28: 18-20፣ የማርቆስ ወንጌል 16: 15-18)፣
- እርሱ ይመራናል እናም ፤ መንገድ ያሳየናል (ዮሐንስ 16:13፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 8:14)፣
- እርሱ መጽናናትን ይሰጠናል (ዮሐንስ 14:18፣ የሓዋርያት ስራ 9:31)፣
- ያሳስበናል እናም ያስተምረናል ( ዮሐንስ 14:26፣ 1 ኛ ቆሮንጦስ 2:11-16)፡
- ከኛ ጋር ይመላለሳል፣ የሕይወታችንም አካል ይሆናል (ዮሐንስ 14:17)፣
- የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ይመሰክራል፣ እናም ስለዚህ በእየሱስ ክርስቶስ ክርስቱ (ከጸጋው) ተካፋዮች ነን (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:16፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:13-14)፣
- እርሱ እግዚአብሔርን ሳንፈራ እንድንቀርበው ነጻነቱን ይሰጠናል (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:15፣2ኛ ቆሮንጦስ 3:17 ፣ 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 2:1-7)።



## ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዝምድና ሊኖርህ ይችላል

በዮሐንስ 14:17፣ እየሱስ እንዲህ ይላል ''***እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ''*** ።

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዝምድና ማድረግ ማለት፣ መኖሩንና በሕይወትህ ዉስጥ አገልግሎቱን መቀበል ነው። ስለዚህ በእርሱ መኖር መካከል ጊዜ ማሳለፍና መቀራረብ አለብህ፣ እንዲሁም እንደ ጓዋደኛህ ልታዉቀው ያስፈልጋል። ይህንን ዝምድና ከእርሱ ጋር በጸሎት ጊዜ በማሳለፍ ፣ ቃሉን በማጥናት ፣ ጥሪዉን በመቀበል ታገኘዋለህ።

እንደገና ከተወለድክ ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ተጠምቀኃል። መጠመቅ ማለት ሙሉ በሙሉ መጥለቅ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ የላስቲክ ኳስ ዉሰድ እናም ወደ ዉሃ ገንዳ ዉስጥ እስከሚጠልቅ ድረስ ወደ ዉስጥ ጨምረው። ዳግመኛ ስትወለድ እንደዚሁ ነው የሚሆነው ፣ ልክ እንደ ኳሱ በመንፈስ ቅዱስ ዉስጥ ትጠልቃለህ። ነገር ግን እንደምታዉቀው፣ በዉሃ ዉስጥ መሸፈን አንድ ነገር ነው ፣ እናም በዉሃ መሞላትና መሸፈን ደሞ ሌላ ነገር ነው። ኳሱ በዉሃ እንዲሞላ ዉሃው የሚያልፍበት ቀዳዳ ሊኖረው ይገባል። በሌላ አነጋገር ኳሱ የተሰራበት ነገር ዉሃን ወደ ዉስጥ ማስገባት የሚፈቅድ መሆን አለበት። በተመሳሳይ መልኩ፣ ዳግመኛ በተወለድክ ግዜ፣ መንፈስ ቅዱስን የግድ በዉስጥህ መቀበል አለብህ እናም በርሱ መሞላት አለብህ።

እንደገና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በሕይወትህ አንድ ግዜ የሚሆን ልምድ አይደለም። ነገር ግን ቀጣይና ቀን በቀን የሚደረግ ልምምድ ነው (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5:18)። ይህ የእርሱን መኖር ማወቅህንና አገልግሎቱን በሕይወትህ መቀበልህን ያመለክታል። ከሱ ጋር የምታደርገው መቀራረብ በምስጋና፣ በጸሎት፣ ቃሉን በማጥናትና ትእዛዙን በጽናት በማክበር በመንፈሱ ልትመራ ትችላለህ።

## በሌላ ቋንቋ መናገር

ከዚህ በፊት እንደገለጽኩት፣ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ልጆች በሌላ ቋንቋ እንዲናገሩ ችሎታን ይሰጣል። እግዚአብሔር እንዳለው፣ ከምልክቶች ሁሉ አንደኛው፣ አማኞችን በመቀጠል የሚከተለው በአዲስ ቋንቋ መናገር መቻል እንዳለባቸው ነው( የማርቆስ ወንጌል 16: 17)።

ይህ መንፈሳዊና መለኮታዊ ችሎታ በመንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚሰጥ ስጦታ ነው፣ ይህም አማኞች በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩበት ቋንቋ ነው። በሌላ ቋንቋ መናገር አንዳንዴ በመንፈስ መጸለይ ተብሎ ይጠራል። በልሣን ቋንቋ ስንናገር በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ነው የምንነጋገረው (1 ኛ ቆሮንጦስ 14:28)። መንፈሳችንም ይታነጻል (የይሁዳ መልእክት 20)። መንፈሳችን ይበረታታል እንዲሁም ይታደሳል (ትንቢተ ኢሳይያስ 40:3)።

መንፈስ ቅዱስን ከተቀበልክ በኋላ፣ በመረጥክበት ግዜ በልሣን ቋንቋ ልትናገር ትችላለህ። በአንተ ዉስጥ ሆኖ አይናገርም ነገር ግን የመናገር ችሎታን ይሰጥኃል። ስለዚህ በፈለክበት ጊዜ በልሣን ቋንቋ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ትችላለህ።

በልሣን ቋንቋ መናገር ስትጀምር፣ በመለማመድ በጣም ቀልጣፋ ተናጋሪ ትሆናለህ። ይህም ልክ ህጻን ልጅ የመጀመሪያዉን ቃል እንደሚለማመድ ማለት ነው። በብዛት ከተለማመደ፣ በጣም ቀልጣፋ ተናጋሪ ይሆናል። በልሳን መናገርም እንደዚሁ ነው። አዲስ ቋንቋ ነው፣ ነገር ግን መማር አያስፈልግህም፣ በመደጋገም በጣም ቀልጣፋ ተናጋሪ ትሆናለህ። በልሣን ቋንቋ ሁልግዜ ከተናገርክ፣ መንፈሳዊ እድገትህ ይፋጠናል፣ ይህም ወደ ሌላ ስጦታዎችና ወደ እግዚአብሔር መንፈስ መገለጥ ይመራሃል።



# 13 ወደ ቤተ ክርስቲያን ልትሄድ ይገባል

በማቴዎስ ወንጌል 16:18 ፣ እየሱስ ስለ ቤተክርስቲያን እንዲህ ሲል ተናግሯል፣ ይህም የእርሱን አካል በምድር ሳለ ይወክላል።

***''አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል። አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና''*** (1 ኛ ቆሮንጦስ 12: 12-14)።

እየሱስ እራስ ሲሆን እኛ ደግሞ ሌላኛው የሰዉነት ክፍል ነን። ክርስቲያኖች (ዳግመኛ የተወለዱ )፣ የእየሱስ አካል ናቸው፣ እንዲሁም አንደኛው ከሌላኛው ጋር (1 ኛ ቆሮንጦስ 12: 27)። ልክ የሰው ሰውነት በተናጠል እንደማይሰራው ሁሉ፣ የተለያዩ የእየሱስ አካላት በተናጠል በትክክል ሊሰሩ አይችሉም ።ይህም ምክንያቱ እግዚአብሔር የተለያየ ስጦታና ጥሪ ለቤተክርስቲያን አባላት ስለሰጠ ነው ፣ በዛም ቤተክርስቲያኗ ተጠቃሚ ትሆናለች(1 ኛ ቆሮንጦስ 12: 18-24፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:11-12)።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን መካፈል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማሟላት ነው። ይህም በተለያዩ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ለምሳሌ ታኣምራት፣ መዳን፣ ትንቢትን በመናገር በሌሎችም እርስበርሳችን እንድንባረክና እንድንጸና ያስችለናል። የምንማረዉንም ቃል በተሻለ ሁኔታ እንረዳለን ፣ ምስክርነት እንሰማለን አስደናቂ ነገሮችንም እንታዘባለን። በኅብረት መጸለይና ማምለክ፣ ጥምር የመንፈስ ቅዱስ መቀባትን ያስገኛል ይህም ለጉባኤዉ አባላት በተለያየ መልኩ እንድናገለግል ይረዳናል( ዕብራውያን 10:25፣ የሓዋርያት ስራ 1:14፣ መዝሙረ ዳዊት 133:1-2)።

በመንፈስ በተሞላ ቤተክርስቲያን በማትካፈልበት ጊዜ፣ በቃሉ በራስህ ለመጓዝ ከባድ ስራ ይሆንብሃል፣ ነገር ግን በመንፈስ በተሞላ ቤተክርቲያን መካፈል፣ ስለ ቤተክርስቲያኑና ስለ አባሎቹ እንድታውቅ ይረዳሃል። መንፈስህንም ማሳደግ ትችላለህ (የዉስጠኛው ሰው)። ይህም ቃሉን በቀላሉ እንድትማርና ዉጤታማ እንድትሆን ያደርጋሃል።

እንደ ክርስቲያን፣ በኣከባቢህ በሚገኝ ቤተክርስቲያን መሳተፍ አለብህ፣ ዕዉቀትህንም ማዳበር አለብህ። አለበለዚያ፣ እራስህን ከእግዚአብሔር በረከት ትከለክላለህ፣ ከቃሉም ትርቃለህ።

አሁን ዳግመኛ ተወልደሀል እራስህን በማወቅ ተመላለስ።

## በቃሉ ማደግ

መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በመስማት እምነት ይመጣል ይላል። ለመንፈሳዊ እድገትህ እንዲሆን የሚከተሉትን መልእክቶች እንድታነብ አሳስባለሁ። እነዚህ መልክቶች በጥንቃቄ የተዘጋጁና እንዴት ፍሬያማና ዉጤታማ እንድትሆን የሚያስተምሩ፣ እንዲሁም በልብህ ዉስጥ እምነት የሚያኖሩ መልክቶች ናቸው። የራስህን ቅጂ ዛሬ በመዉሰድ በሕይወትህ ሊመጣ የሚችለዉን ለውጥ ተመልከት፥

1. አሁን ዳግመኛ ተወልደሀል (1 ካሴት)፣
2. ክርስትና ሲተነተን (1 ካሴት)፣
3. በቃሉ ማደግ (1 ካሴት)፣
4. ወደ ጉልምስና ማደግ (1 ካሴት)፣
5. መንፈስህን ማነጽ(1 ካሴት)፣
6. በመንፈስ መሞላት (1 ካሴት)፣
7. ድል በዓለም ዉስጥ (1 ካሴት) እና
8. አዲስ መወለድ ተከታታይ መልእክት(12 ካሴት)።



ስለ አገልግሎታችን እንዲሁም በመጋቢ ክሪስ አያኪሒሎም ስለ ተጻፉ መጽሐፍቶችና ካሴቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎን በሚከተለው አድራሻችን ያግኙን።

**CHRIST EMBASSY**

**(የክርስቶስ ኢምባሲ)**

a.k.a. Believers' LoveWorld Inc.

ፍቅር-ዓለም የአማኞች ማህበር

ፖስታ ሳጥን ቁ፣ 21520 London E10 5 FG
United Kingdom

ስልክ/ፋክስ፣ (44) 0181-670-6845
ኢ-ሜይል: christembassy-int@lineone.net

ወይም

ፖስታ ሳጥን ቁ፣ 13563, Ikeja, Lagos, Nigeria
ስልክ: (234) 01-7740109
01-7740243
ፋክስ: (234) 01-4934392
ኢ-ሜይል: storeadmin@loveworldmail.org

ድህረ ገጽ: www.christembassyonlinestore.org